# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ
## ለንደን

# Embassy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia
## LONDON


ቀን ፡ ህዳር 7 ቀን 2013 ዓ.ም.
ቁጥር ፡ ኢ.ኤም.ለ. 199/4/11/2013

**በዩናይትድ ኪንግደምና በሰሜን አየርላንድ ለምትገኙ ኢትጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን**

**ባያላችሁበት**

ከሁለት አመታት በፊት በሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች መስዋዕትነት የመጣውን ለውጥ ለመቀልበስ ሲታገል የቆየው የህወሀት ጁንታ ቡድን መግባባቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲመጡ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ የነበረውን የአገሪቱን መንግስት ትዕግስት ከድክመት በመቁጠር ከጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ምሽት ጀምሮ ከ20 ዓመት በላይ በክልሉ የሀገሩንና የህዝቡን ሰላም በመጠበቅ በኖረው ሰሜን ዕዝ የመከላከያ ሠራዊታችን ላይ ባልተጠበቀ ሁኔታ በፈጸመው ኢሰብአዊ ድርጊት ጸረ ህዝብነቱን በማሳየቱ መንግስት በክልሉ የህግ ማስከበር እርምጃ መውሰዱ ይታወቃል፡፡

ይህንን ያልተጠበቀና ሠራዊታችንን ለከፍተኛ መስዋዕትነት የዳረገ አስከፊ ድርጊት በመቃወም በዩናይትድ ኪንግደምና በሰሜን አየርላንድ የምትገኙ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት መንግስት እየወሰደ ያለውን እርምጃ በመደገፍ ለመከላከያ ኃይላችን ድጋፋችሁን ለማድረግ ፍላጎታችሁን በገለጻችሁልን መሠረት ከኤምባሲው ጋር በጋራ የሚንቀሳቀስ ግብረኃይል ተመስርቶ እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡

በመሆኑም ዳያስፖራው በሚኖርበት ኮንስቲትወንሲ ለፓርላማ አባላት አገራችን እየወሰደች ያለችውን ህግን የማስከበር እርምጃ ትክክለኛነት በማስረዳት እና በማህበራዊ ሚዲያዎች የሚቀርቡ አፍራሽ አሉባልታዎችን በመመከት እያደረጋችሁ ያላችሁትን ጥረት እንድትቀጥሉ እየጠየቅን በዚህ በህወሀት ቀስቃሽነት በተጀመረው ጦርነት ለተጎዱ የሠራዊት አባላትና ቤተሰቦቻቸው ከዚህ ቀጥሎ በኤምባሲው በተከፈተ የባንክ አካውንት የቻላችሁትን የገንዘብ መጠን እንድትለግሱ በአክብሮት እየጠየቅን ተጨማሪ መረጃ ካስፈለጋችሁ በስልክ ቁጥሮች 07367109262/ 07939956086/07575827053 መደወል የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

Account Name: Embassy of Ethiopia
Bank Name: Lloyds Bank
Account Number: 43178968
Sort Code: 306541
Reference: National Army Veterans Support Fund (NAV Support Fund)

ከሠላምታ ጋር

ተፈሪ መለሰ
አምባሳደር


17 PRINCES GATE
LONDON, SW7 1PZ
www.ethioembassy.org.uk

TEL: 020 7589 7212
FAX: 020 7584 7054
e-mail: info@ethioembassy.org.uk